# ፈረስ ነህ ይጋልቡህ!!



ቃል ኪዳን ካልጠበክ ፣ የታሪክ አደራ፣

ሁሌ እያዋረዱ ፣ ሲገሉህ በተራ፣

ተገትረክ ከቆምክ ፣ አሻፈረኝ ካላልክ፣

ወያኔን ገርስሰህ ፣ እንደድር ካላበርክ፣

ፈረስ ነህ ይጋልቡህ ፣ አህያነህ ይጫኑህ::

ግንባሩን ለጥይት ፣ ላንተ የተደፋልህ፣

ኢትዮጵያን ብሎ ፣ ላንተ የተሰዋልህ፣

ጴጥሮስ ሲነሳ፣ ግዴታ ካልሰጠህ፣

አይነሳም ብለህ ፣ ቆርጠህ ካልተታገልክ፣

እምቢ አሻፈረኝ፣ ነጻነቴን ካላልክ፣

ፈረስ ነህ ይጋልቡህ ፣ አህያነህ ይጫኑህ!!

ታሪክህን ሲያፈርስ ፣ ባቡር ሊያሳፍርህ ?

ቆመህ ከተገተርክ ፣ ጴጥሮስን ካላልክ፣

ባንዲራዬን ሳትል ፣ ለሆድህ ከሰገድክ፣

ሰብዓዊነትህን ፣ በቁመናህ ከሸጥክ ፣

አንዴም ብቻ ሳይሆን ፣ የሞት ሞትን ከሞትክ፣

ፍርሃት ከወጠረህ ፣ ኢጋዚ ካስፈራህ ፣

ለሚበሰብሰው ፣ ለስጋህ ከፈራህ ፣

ፈረስ ነህ ይጋልቡህ ፣ አህያነህ ይጫኑህ ፣

ፈረስ ነህ ይጋልቡህ ፣ አህያነህ ይጫኑህ ፣

መይሳው ከምድረ ስዊድን

2013-05-03